# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን

## የ1997 በጀት ዓመት
## የስታቲስቲክስ የሥራ ዕቅድ

ሐምሌ 1996
አዲስ አበባ

7

# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን

## የ1997 በጀት ዓመት
## የስታቲስቲክስ የሥራ ዕቅድ

ሐምሌ 1996
አዲስ አበባ

# ማውጫ


| አርዕስት | | ገጽ |
|---|---|---|
| 1. | መግቢያ | 1 |
| 2. | በ1997 የሚካሄዱ ጥናቶች ዓላማዎችና የአፈፃፀም ስልቶች | 2 |
| | 2.1 የጥናቶች ዓላማ | 2 |
| | 2.2 የጥናቶች ስልት | 2 |
| 3. | የ1997 ዕቅድ ይዘት | 3 |
| | 3.1 በ1997 ለማካሄድ የታቀዱ ጥናቶች | 3 |
| 4. | በ1997 ዓ.ም የመንግስትና የውጪ ዕርዳታ በጀት መግለጫ | 4 |
| | 4.1 የመንግስት ካፒታል በጀት ፍላጎት | 4 |
| | 4.2 የመንግስት ካፒታል በጀት መግለጫ | 5 |
| | 4.3 የውጪ ዕርዳታ በጀት ፍላጐት | 9 |
| | 4.4 የውጪ ዕርዳታ በጀት መግለጫ | 9 |
| 5. | የ1997 የመንግስት ካፒታልና የውጪ ዕርዳታ በጀት ፍላጎት | 10 |
| | 5.1 የመንግስት ካፒታል በጀት ፍላጐት ማጠቃለያ | 10 |
| | 5.2 የመንግስት የካፒታል በጀት ፍላጐት በወጪ ዓይነት | 10 |
| | 5.3 የውጪ ዕርዳታ በጀት ፍላጐት ማጠቃለያ | 11 |
| | 5.4 የውጪ ዕርዳታ በጀት ፍላጐት በወጪ ዓይነት | 11 |
| 6. | የ1997 ጥናቶች ግብና መግለጫ | 11 |
| | 6.1 የጥናቶች ግብ | 11 |
| | 6.2 የጥናቶች ዝርዝር መግለጫ | 12 |
| 7. | የ1997 የሰው ኃይል ፍላጎት | 26 |
| 8. | የ1997 የጥናቶች መርሃ ግብር | 26 |
| 9. | ትኩረትና መመሪያ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች | 41 |

# የ1997 በጀት ዓመት
# የስታቲስቲክስ የሥራ ዕቅድ

## 1. መግቢያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የአገሪቱን የስታቲስቲክስ መረጃ ፍላጎት በማሟላት ረገድ ያለበትን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችል በየዓመቱ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥናቶችን በማካሄድ ላይ ይገኛል። በዚህም መሠረት መ/ቤቱ ለስታቲስቲክስ መረጃ ዕድገት አመቺ ሁኔታን በመፍጠርና በየጊዜዉ የተሻሻሉ የአሠራር ዘዴዎችን በመቀየስ የመረጃ ፍላጎትን ክፍተት ለማጥበብ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል።

በ1997 በጀት ዓመት መ/ቤቱ የመንግሥትን የልማት ትኩረት አቅጣጫና የመረጃ ተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የተለያዩ ጥናቶችን ለማካሄድ ዕቅድ ይዟል። እነዚህ በዕቅድ የተያዙ ጥናቶች አገሪቱ ለምታካሂደዉ የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ አተገባበር ስኬታማነት፣ ክትትልና ግምገማ የሚረዱ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን የሚዳስሱ መረጃዎችን የሚያስገኙ ናቸዉ። እንደዚሁም አገሪቱ በምትከተለዉ ገበያ መር የኢኮኖሚ አቅጣጫ ፈጣን ለዉጥና ዕድገት የሚታይባቸዉ የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ወቅታዊ ሁኔታ ለመከታተልና ለመገምገም የሚጠቅሙ መረጃዎችን ያስገኛሉ።

ይህ የ1997 በጀት ዓመት የካፒታል ፕሮጀክት ዕቅድ በዘጠኝ የተለያዩ ክፍሎች የቀረበ ሲሆን፤ በክፍል አንድ መግቢያ፣ በክፍል ሁለት ደግሞ የ1997 ዕቅድ ዓላማዎችና የአፈፃፀም ስልቶችን ለማቅረብ ተሞክሯል። በክፍል ሦስት የ1997 ዕቅድ ይዘት የተብራራ ሲሆን፤ በክፍል አራት ደግሞ ለታቀዱት ጥናቶች ማስፈፀሚያ የሚዉል የመንግሥት ካፒታልና የውጪ ዕርዳታ በጀት ፍላጎትና መግለጫ ቀርቧል። እንደዚሁም ከክፍል አምስት እስከ ስምንት ድረስ የ1997 የመንግስት የካፒታልና የውጪ ዕርዳታ በጀት ፍላጎት በወጪ ዓይነት፣ የ1997 የዕቅድ ግብ፣ የሰው ኃይል ፍላጎትና የዕቅዱ መርሃ-ግብር በቅደም ተከተል እንዲካተት ተደርጓል። በክፍል ዘጠኝ የ1997 በጀት ዓመት ዕቅድን ተግባራዊ ለማድረግ በበላይ አካል ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች እንዲካተቱ ተደርጓል።

## 2. በ1997 በጀት ዓመት የሚካሄዱ ጥናቶች ዓላማዎችና የአፈፃፀም ስልቶች

### 2.1 በ1997 በጀት ዓመት የሚካሄዱ ጥናቶች ዓላማ

በ1997 በጀት ዓመት የሚካሄዱ ጥናቶች ዓላማዎች ከመ/ቤቱ ራዕይና ተልዕኮ ጋር የተቀናጁ ሆነዉ የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡፡

- ለፕላን ዝግጅት፣ ለክትትልና ግምገማ፣ ለምርምር፣ ለፖሊሲ ቀረፃና ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች ሊያገለግሉ የሚችሉ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጃዎችን በተቀናጀ አሠራር ሰብስቦ፣ አቀነባብሮና ተንትኖ ለተጠቃሚዎች ማሰራጫት፣

- በመካሄድ ላይ ያሉትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የልማት ሥራዎች እንዲሁም በመንግስትና በግሉ ዘርፍ የሚካሄዱ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ሊያግዝና ሊደግፉ የሚችሉ ወቅታዊ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ሰብስቦ፣ አቀነባብሮና ተንትኖ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ማቅረብ፣እና

- አገራዊ የስታቲስቲክስ የመረጃ ፍላጎት ከማሟላት አኳያ አመቺና ተስማሚ የሆኑ የስታቲስቲክስ ሥራዎች ማከናወን ናቸው፡፡

### 2.2 የጥናቶች አፈጻጸም ስልት

- የአገሪቷ የስታቲስቲክስ ሥራ ጥራትና ደረጃዉ የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ይቻል ዘንድ የባለሥልጣኑ መ/ቤት አቅሙን ለማጎልበት ጥረት ማድረግ፣

- ከተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ጋር የሚኖረዉን የሥራ ግንኙነት በማጠናከር በተለይም ሕብረተሰቡ የስታቲስቲክስ መረጃ አስፈላጊነትና ጥቅም በሚገባ ተረድቶ ትክክለኛ መረጃ በመስጠት ረገድ ትብብር እንዲያደርግ በተለያዩ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ተገቢዉን ትምህርትና ቅስቀሳ ማድረግ፣

- የስታቲስቲክስ የአሠራር ዘዴን በማሻሻል የመረጃ መሰብሰብ፣ ቅንብርና ትንተና ሥራ በሙያዉ የሰለጠነ የሰዉ ኃይል ስለሚያስፈልግ በዚህ በኩል የሚመደብ ሠራተኛ በአገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ አገር እንዲሰለጥን ማድረግ፣እና

- የባለሥልጣኑ መ/ቤት ከተለያዩ የዉጭ አገር መንግሥታት፣ የዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር በቀጥታም ሆነ በሚመለከታቸዉ የመንግሥት አካላት በኩል ግንኙነት በመፍጠርና ብሎም በማጠናከር ለጥናቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ማስገኘት፣ የሥልጠናና የፋሲሊቲዎች ድጋፍ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ናቸዉ።

## 3. <u>የ1997 በጀት ዓመት ዕቅድ ይዘት</u>

በ1997 በጀት ዓመት በብሔራዊ የተቀናጀ ስርቬይ ፕሮግራም ስር እና በውጪ ዕርዳታ በርካታ ጥናቶችን ለማካሄድ መ/ቤቱ በዕቅድ ይዟል። እነዚህ ጥናቶች ከአምስት ዓመቱ የስታቲስቲክስ ፕሮግራም ላይ የተወሰዱ ሲሆኑ፤ የመንግሥትንና የውጪ ዕርዳታ የበጀት አመዳደብና የመ/ቤቱን የማስፈፀም አቅም ግምት ዉስጥ በማስገባት ጥናቶቹን በበጀት ዓመቱ ለማካሄድ ታስቧል። በመሆኑም በ1997 በጀት ዓመት የሚጠኑ ጥናቶች ዝርዝር የሚከተሉት ናቸዉ። እነዚህም፡-

### 3.1 <u>በ1997 ለማካሄድ የታቀዱ ጥናቶች</u>
<u>ብሔራዊ የተቀናጀ ስርቬይ ፕሮግራም</u>

#### 3.1.1 የግብርናና የተፈጥሮ ሃብት ስታቲስቲክስ

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት /በገጠር/
- የሰብል ምርት ናሙና ጥናት በመኸር ወቅት /በገጠር/
  - የታረሰ መሬት ስፋትና የሰብል ምርት መጠን ጥናት
  - የመሬት አጠቃቀም ጥናት
  - የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ጥናት
- የሰብል ምርት ናሙና ጥናት በበልግ ወቅት /በገጠር/
  - የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን ጥናት
  - የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ጥናት
- የሰፋፊ የግል፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎች ጥናት /በገጠር/
- የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ኃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናት /በገጠር/
- የቋሚ ሰብሎች አትክልትና ሥራ ሥር ተክሎች ምርታማነት (yield) ጥናት /በገጠር/

3.1.2 የኢንዱስትሪ፣ ንግድና ትራንስፖርት ስታቲስቲክስ

- የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት /በከተማ/
- ወቅታዊ የማምረቻ፣ የንግድና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት /በየስድስት ወራት/በከተማ/
- የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የምርት መጠንና የአምራቾች ዋጋ ጥናት (በየሩብ ዓመቱ) /በከተማ/
- የኢኮኖሚያዊ ድርጅቶችን ዝርዝር ወቅታዊ ማድረግ /updating business register/
- የውጪ ንግድ ስታቲስቲክስ መረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር
- የትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ መረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር
- የምርት መጠንና የአምራች ዋጋ ኢንዴክስ ዝግጅት /በዋናው መ/ቤት/

3.1.3 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ

- የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት /በገጠር/
- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት /በከተማ/
- የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክሶች ዝግጅት /በዋናው መ/ቤት/
- የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት (2ኛ ዙር)
- ተሳትፏዊ የድህነት ሁኔታ ዳሰሳ ጥናት

3.1.4 የማህበራዊ ስታቲስቲክስ

- የጎዳና ተዳዳሪ ህፃናት ጥናት /በገጠርና በከተማ/
- ወላጅ አልባ ህፃናት ጥናት /በከተማ/
- የሰው ኃይል ጥናት /በገጠርና በከተማ/

3.2 ከ1997 በጀት ዓመት የዞሩ ጥናቶችን የመረጃ ቅንብር ሥራ ማከናወን

## 4. <u>በ1997 ዓ.ም የመንግስትና የውጪ እርዳታ በጀት መግለጫ</u>

### 4.1 <u>የመንግስት ካፒታል በጀት ፍላጎት</u>

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1997 በጀት ዓመት ለሚያካሂዳቸው ጥናቶች ማስፈጸሚያ በተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር 32,871,200 ከመንግሥት ግምጃ ቤት እንዲመደብለት ተደርጐአል፡፡

## 4.2 የመንግስት ካፒታል በጀት መግለጫ

በ1997 በጀት ዓመት ለሚጠኑ ጥናቶች የተያዘዉ የካፒታል በጀት ፍላጎት በአንድ ፕሮግራም ጥላ ስር የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን በሚያስችል መንገድ ሲሆን፤ በጣም ወጪ ቆጣቢና በአጭር ጊዜ ዉስጥ በተለያዩ ጥናቶች የመስክ ሠራተኞችን በአንድ ጊዜ በማሰማራት ሥራቸዉን እንዲያከናዉኑ በሚያስችል መልኩ ነዉ:: በመሆኑም የበጀት ፍላጎቱ ጥያቄ የቀረበዉና የተሰላዉ ቀጥሎ ያሉትን ሁኔታዎች ግንዛቤ ዉስጥ በማካተት ነዉ::

### ሀ/ አጠቃላይ ታሣቢዎች

- በበጀት ዓመቱ መረጃ የሚሰበሰብባቸዉ የቆጠራ ቦታዎች በገጠር 2,072 እና በከተማ 790 በድምሩ 2,827 ሲሆኑ፤ በ106 ከተሞች ላይ በተመረጡ 119 የገበያ ቦታዎች የአገልግሎቶችና የችርቻሮ ዋጋ ጥናት መረጃ በተናጠል ይሰበሰባል:: እንዲሁም የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ከየድርጅቶቹ መረጃዉ ይሰበሰባል::

- ለአንድ ጊዜ በተቀጠሩ (ወደ መስክ በገቡ) መረጃ ሰብሳቢዎች የተለያዩ የጥናት መጠይቆች እንዲሞሉ የሚደረግ ሲሆን፤ የመስክ ተቆጣጣሪዎችም በተመሣሣይ ሁኔታ የቁጥጥር ሥራቸዉን ለሁሉም ጥናቶች እንዲያካሂዱ ይደረጋል:: ሆኖም የጥናቱ መረጃ የሚሰበሰብበት ጊዜ የተለያየ ከሆነ ወይም ለጥናቶቹ የተመረጡት የቆጠራ ቦታዎች የተለዩ ከሆኑ መረጃ ለመሰብሰብ የሚወስደዉ ጊዜ ግምት ዉስጥ በማስገባት አዲስ ሠራተኞች ይቀጠራሉ (የአገልግሎቶችና የችርቻሮ ዋጋ ጥናት)::

- የጥናት ሪፖርቶቹ በገጠርና በከተማ በዞን ደረጃ ሪፖርት የሚወጣላቸዉ ሲሆን፤ እንደ ጥናቶቹ ሁኔታ በክልልና በአገር አቀፍ ደረጃም ሪፖርቶቹ እንዲወጡ ይደረጋል::

### ለ/ የበጀት ርዕስ ማብራሪያ

- በደመወዝ የወጪ አርዕስት /6113/ የተጠየቀዉ በጀት ለፕሮጀክቱ ሥራ በኮንትራት ለሚቀጠሩ ሠራተኞች የወር ደመወዝ ሲሆን፤ በተጨማሪም በአነስተኛ የደመወዝ ልዩነት ክፍያ ቋሚ የመስክ ሠራተኞችን (ከመረጃ

ሰብሳቢነት ወደ ተቆጣጣሪነት) ከያዙት የሥራ መደብ ከፍ በማድረግ የደመወዙን ልዩነት ከፕሮጀክቱ ለመክፈል የተጠየቀ ነዉ፡፡

- በሰዉ ጉልበት የወጪ አርዕስት (6114) የተጠየቀዉ መረጃ ሰብሳቢዎች በተመደቡበት አካባቢ የቆጠራ ቦታ ካርታ ድንበር ለሚለዩላቸዉ፣ ሜትር በመያዝ ለመለካት ለሚረዱዋቸዉ፣ እንዲሁም ሚዛን ለሚሸከሙላቸዉና ለመመዘንም ለሚያግዟቸዉ የቀን ሠራተኞች ክፍያ ወጪ የተጠየቀ ነዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዋናዉ መ/ቤት ላለዉ ማተሚያ ቤት በተለያዩ መሣሪያዎች ላይ ለሚሰሩና በመረጃ ማቀነባበሪያ መምሪያ መረጃ የተሰበሰበባቸዉን ዶክመንቶች ከመጋዘን ወደ ኮምፒዉተር ክፍልና ከኮምፒዉተር ክፍል ወደ መጋዘን ለሚያመላልሱ የቀን ሠራተኞች የሚከፈል ሲሆን፣ ለሁሉም የቀን ሠራተኞች ክፍያዉ የተሰላዉ በቀን ሰባት ብር ሂሣብ ነዉ፡፡

- በበረሃና በመጠለያ አበል የወጪ አርዕስት (6123) የተጠየቀዉ በጀት በፌዴራልና በክልል ደረጃ የአካባቢዉ ሁኔታ ለሥራ ከፍተኛ አስቸጋሪ የአየር ፀባይ ያለዉ በመሆኑ የበረሃ አበል የሚያስፈልገዉ እንደሆኑ የተረጋገጠላቸዉ ቦታዎች ሲሆኑ፣ የቆጠራ ቦታዎቹም በናሙና ሲመረጡ እነዚህ አካባቢዎች ስለተመረጡ መረጃ ሰብሳቢዎችም ስለሚመደቡበት የደመወዛቸዉ 30% ተሰልቶ የቀረበ ነዉ፡፡ እንዲሁም በገጠርና በከተማ የሚሰማሩት መረጃ ሰብሳቢዎች ኑሮአቸዉን በአካባቢዉ ስለሚያደርጉ ለአነስተኛ ቤት (ለመኖሪያና ለመስክ ቁሣቁስ ማስቀመጫ) ኪራይ እንዲሆናቸዉ በወር 30 ብር ታስቦ የተጠየቀ በጀት ነዉ፡፡

- በጽሕፈት መሣሪያ የወጪ አርዕስት (6212) የተያዘዉ በፕሮጀክቱ ለሚሰማሩ የመስክ ሠራተኞች፣ ባለሙያዎችና ሌሎች ቴክኒሽያኖች በሥልጠና ወቅት፣ በሥራ ስምሪትና ለቢሮ አገልግሎት ለሚወሰዱ የተለያዩ የጽ/ቤት አላቂ ዕቃዎች የተጠየቀ በጀት ነዉ፡፡ (ዝርዝሩ በዕዝል አንድ ላይ ቀርቧል)

- በሕትመት የወጪ አርዕስት (6217) የተጠየቀዉ መ/ቤቱ የራሱ ማተሚያ ቤት ያለዉ በመሆኑ ለጥናቶቹ የሚያገለግሉ መጠይቆች፣ መመሪያዎችና የጥናት ሪፖርቶች ታትመዉ የሚወጡት ከዚሁ ክፍል ነዉ፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ለሚገዙ የሕትመት ዕቃዎች የሚያስፈልግ በጀት ተሰልቶ በዚህ ርዕስ ቀርቧል፡፡ (ዝርዝሩም በዕዝል ሁለት ላይ ቀርቧል)፡፡

- በነዳጅና ቅባት የወጪ አርዕስት (6217) የተጠየቀዉ በጀት መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸዉ ጥናቶች የመስክ ሠራተኞችን ስምሪትና ቁጥጥር የሚያስፈዕመዉ ባሉት 200 የመስክ ተሽከርካሪዎች በመጠቀም ነው፡፡ ለእነዚህ ተሽከርካሪዎች የሚሆን ነዳጅና ቅባት በጥናቱ ወቅት በሚጓዙት ኪ.ሜትር ታስቦ የቀረበ ነዉ፡፡ አንድ ተሽከርካሪ በአንድ ሊትር (በሦስት ብር) አምስት ኪሎ ሜትር እንደሚሄድና ለእያንዳንዱ ኪሎ ሜትር 0.10 ሣንቲም የቅባት ወጪ በማሰብ የተሰላ በጀት ነዉ፡፡

- በዉሎ አበል የወጪ አርዕስት (6231) የተጠየቀዉ በጀት ለሚካሄዱት ጥናቶች ከሥልጠና ጀምሮ የሪፖርት ዉጤት ለተጠቃሚዎች እስከሚቀርብበት ጊዜ ድረስ ለኮንትራትና ለቋሚ ሠራተኞች የሚከፈል የዉሎ አበል ነዉ፡፡ ለሁሉም ጥናቶች መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት ከተቆጣጣሪዎች ጀምሮ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ድረስ ስለሥራዉ ሂደት የቁጥጥር ተግባር ስለሚያካሂዱ ጥያቄዉ ቀርቧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለወጪ ቁጠባ ሲባል አንድ ተቆጣጣሪ በሁሉም ጥናቶች የሚሳተፉ የመረጃ ሰብሳቢዎችን እንዲቆጣጠሩ ይደረጋል፡፡ ይህም በመሆኑ መንግሥት ከፈቀደዉ የዉሎ አበል መክፈያ ቀናት (90 ቀናት) በላይ መስክ ላይ ይቆያሉ፡፡ ይህ ካልተደረገ ደግሞ መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸዉ በርካታ ጥናቶች የተለያዩ ተቆጣጣሪዎችን መቅጠር ሊያስፈልግ ነዉ፡፡ ሆኖም መ/ቤቱ ይህን ግምት ዉስጥ በማስገባት አንድ ተቆጣጣሪ በተለያዩ ጥናቶች ላይ የተሣተፉ (የሚሰሩ) የመረጃ ሰብሳቢዎች ሥራ እንዲቆጣጠር ተደርጓል፡፡ በዚህም የውሎ አበሉ ቀናት ከ90 ቀናት በላይ ሆኖ ቀርቧል፡፡

- በትራንስፖርት ክፍያ የወጪ አርዕስት (6232) ላይ የተጠየቀዉ በጀት መረጃ ሰብሳቢዎች ወደ ተመደቡበት ቆጠራ ቦታ ሲገቡ ለሁሉም ተሽከርካሪ ማቅረብ የማይቻል በመሆኑ የትራንስፖርት ወጪ በማስፈለጉ፤ ተቆጣጣሪዎች ተሽከርካሪ በማይደርስባቸዉ የቆጠራ ቦታዎች ላይ የበቅሎ ኪራይ ስለሚከፈልላቸዉ፣ ባለሙያዎችና የሥራ ኃላፊዎች ለቁጥጥር ሲወጡ የአየርና የአዉቶቡስ ትራንስፖርት ስለሚጠቀሙ የተጠቀሱትን ወጪዎች ለመሸፈን የቀረበ በጀት ነዉ፡፡

- በትራንስፖርት ጥገና የወጪ አርዕስት (6241) የቀረበዉ በጀት መ/ቤቱ ለሚጠቀምባቸዉ 200 ተሽከርካሪ ወርሃዊ የጥገና ወጪና ለአንድ ዓመት የሚያስፈልጋቸዉ የጎማ ፍጆታ ለመሸፈን የቀረበ ነዉ፡፡

- በመሣሪያ ጥገና የወጪ አርዕስት (6243) የቀረበዉ በጀት መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸዉ ጥናቶች የሚጠቀምባቸዉ የተለያዩ መጠን ያላቸዉ ኮምፒዉተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ የሕትመት መሣሪያዎች፣ የሂሣብ መኪናዎችና ሌሎች የቢሮ ዕቃዎችን ለማስጠገን እንዲቻል የቀረበ ጥያቄ ነዉ።

- በቢሮና ለሥልጠና አዳራሽ ኪራይ የወጪ አርዕስት (6252) የተጠየቀዉ ለአሥራ ስምንት ቅ/ጽ/ቤቶች የዓመት የቢሮ ኪራይ እንዲሁም ለሃያ አምስቱ ቅ/ጽ/ቤቶችና ለዋናዉ መ/ቤት ለመረጃ ሰብሳቢዎችና የመስክ ሠራተኞች በየጥናቶቹ ለሚሰጥ ስልጠና የአዳራሽ ኪራይ በስልጠናዉ ቀንና ለአንድ ቀን በሚያስከፍሉት ዋጋ ተሰልቶ የቀረበ ጥያቄ ነዉ።

- በኢንሹራንስ የወጪ አርዕስት (6254) የተጠየቀዉ ለመ/ቤቱ የመስክ ተሽከርካሪዎች ለዓመታዊ የመድን ዋስትና ሽፋን እንዲሁም በየጥናቱ ላይ ለሚሣተፉ ቋሚና ኮንትራት ሰራተኞች መስክ በሚቆዩበት ጊዜ ለሚደርስ አደጋ የመድን ሽፋን ጥናቶቹ በሚወስዱት ጊዜ ተሰልቶ የቀረበ ጥያቄ ነዉ።

- በኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ የወጪ አርዕስት (6257) የተጠየቀዉ በጀት ለሃያ አምስቱ ቅ/ጽ/ቤቶች የመብራት አገልግሎት ክፍያ በወር ለአንድ ጽ/ቤት በ150 ብር ሂሣብ ተሰልቶ የቀረበ ነዉ።

- በስልክ አገልግሎት ክፍያ የወጪ አርዕስት (6258) የተጠየቀዉ ለዋናዉ መ/ቤት የኢንተርኔት አገልግሎት ክፍያ ለሁለት ሰርቨሮች የወር ኪራይ እንዲሁም ለ25ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች የስልክና ፋክስ አገልግሎት ክፍያ የተጠየቀ በጀት ነዉ።

- ለፖስታ፣ ዉሃና ሌሎች አገልግሎት ክፍያ (6259) የቀረበዉ ዋናዉ መ/ቤት ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ ለሚያደርገዉ የገንዘብ መላላክ ተግባር ለባንክ ኮሚሽን እንዲሁም ለ25ቱም ቅ/ጽ/ቤቶች ለፖስታ፣ ዉኃና ሌሎች አገልግሎት ክፍያ የተጠየቀ በጀት ነዉ።

- በሥልጠና የወጪ አርዕስት (6271) የተጠየቀዉ አብዛኛዎቹ ቅ/ጽ/ቤቶች በሰዉ ኃይል እየተሟሉ የሚገኙት ባለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ ነዉ። እነዚህን ሠራተኞች በተለያዩ ሙያ የሥራ ላይ ሥልጠና ለመስጠትና በዋናዉ መ/ቤትም ተመሣሣይ ሥልጠና ላላገኙ ሠራተኞች ለአጫጭር ቀናት ሥልጠናዎች የተጠየቀ ወጪ ነዉ።

## 4.3 የውጪ ዕርዳታ በጀት ፍላጎት

በመ/ቤቱ በ1996/97 ለሚካሄዱ ሁለት ጥናቶች ማስፈጸሚያ እና ለአቅም ግንባታ ሥራዎች ለአምስት ዓመት ከውጪ ዕርዳታ 31,495,925 ብር ተመድቧል።

## 4.4 የውጪ ዕርዳታ በጀት መግለጫ

በ1996/97 በጀት ዓመት ለሚጠኑ ሁለት ጥናቶች የተያዘው በጀት የተሰላው ቀጥሎ ያሉትን ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ በማካተት ነው።

### አጠቃላይ ታሣቢዎች

- ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት በአገር አቀፍ ደረጃ በናሙና በተመረጡ ከ2,862 የቆጠራ ቦታዎች 37,504 ቤተሰቦች (በገጠር 24,864 እና በከተማ 12,640) በጥናቱ እንደሚሸፈኑ፣ እንዲሁም ለቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት በአገር አቀፍ ደረጃ በናሙና በተመረጡ በ1,620 በቆጠራ ቦታዎች 22,600 ቤተሰቦች (በገጠር 9,960 እና በከተማ 12,640) በጥናቱ እንደሚሸፈኑ ተገምቶ ነው።

- የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት ሪፖርቶች በክልልና በዞን ደረጃ ሪፖርት የሚወጣ ሲሆን፤ የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት በክልል ደረጃ ሪፖርት ይወጣል።

### የበጀት ማብራሪያ

- የሰው ኃይል ልማት በሚል የወጪ ርዕስ ስር የተጠቀሰው በጀት በመ/ቤቱ ያሉ ባለሙያዎችን በተለያዩ የስታቲስቲክስ ሙያዎች በውጭ አገር የረጂምና የአጭር ጊዜ ስልጠና ለመስጠት ታስቦ ሲሆን፣ በሴሚናርና አውደ ጥናት የወጪ ርዕስ የተያዘው ከጥናቶቹ በፊትና በኋላ በየደረጃው ከሚገኙ የመረጃ ተጠቃሚዎች ጋር ለሚደረግ የምክክር ስብሰባ የሚውል ነው።

- ለትራንስፖርትና ሌሎች ወጪዎች ስር የተጠቃለለው ባለሙያዎች፣ የመስክ ሠራተኞችና መረጃ ሰብሳቢዎች በየብስና በአየር ለሥራ በሚንቀሳቀሱበት

ወቅት ለትራንስፖርት የሚከፈል ሲሆን፤ ለትራንስፖርትና ለጥገና የተያዘው ለነዳጅና ለተሽከርካሪ ጥገና የሚውል በጀት ነው።

- በቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ የታየው በጀት የመ/ቤቱ ሎጂስቲክስ ለማጠናከር የመስክ ተሽከርካሪዎች፣ የተለያዩ ቋሚ የመስክ ዕቃዎች፣ የቢሮ መገልገያዎች እንዲሁም አላቂ የጽ/መሣሪያ ግዥን ለማካሄድ የተያዘ በጀትን ያጠቃልላል። በተመሣሣይ በሌሎች ወጪዎች አርዕስት የታየው ለኢንሹራንስ፣ ፖስታ፣ ስልክና ሌሎች ወጪዎች መሸፈኛ እንዲውል የተያዘ በጀት ነው።

## 5. የ1997 የመንግሥት ካፒታልና የውጪ ዕርዳታ በጀት ፍላጎት በወጪ ዓይነት

### 5.1 የመንግስት ካፒታል በጀት ፍላጎት ማጠቃለያ

በ1997 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለሚያካሂደዉ የተቀናጀ ስርቬይ ፕሮግራም በጠቅላላዉ 32,871,200 ብር የካፒታል በጀት ጥያቄ የቀረበ ሲሆን፤ ዝርዝሩም እንደሚከተለዉ ቀርቧል።

### 5.2 ለብሔራዊ የተቀናጀ ስርቬይ ፕሮግራም በጀት በወጪ ዓይነት

- ለደመወዝ ብር 14,148,000
- ለሰው ጉልበት ወጪ ብር 1,033,000
- ለአበል ብር 379,000
  - ለበረሃ አበል ብር 379,000
- ለአላቂ ጽ/መሣሪያ ብር 200,000
- ለሕትመት ብር 336,000
- ለነዳጅና ቅባት ብር 2,010,700
- ለውሎ አበል ብር 11,369,000
  - ለሥልጠና ብር 5,579,616
  - ለመስክ ሥራ ብር 5,789,384
- ለትራንስፖርት ክፍያ ብር 433,000
  - ለተሽከርካሪ ብር 248,200
  - ለአውሮፕላን ብር 60,800
  - ለበቅሎ ብር 124,000
- ለተሽከርካሪ ጥገናና ጎማ ግዢ ብር 1,240,000
  - ለተሽከርካሪ ጥገና ብር 840,000
  - ለጎማ ግዢ ብር 400,000
- ለመሳሪያ ጥገና ብር 45,000
- ለኪራይ ብር 263,000
  - ለጽ/ቤቶች ኪራይ ብር 263,000

- ለኢንሹራንስ ብር 939,500
  - ለተሽከርካሪዎች ብር 396,000
  - ለመስክ ሠራተኞች ብር 543,500

- ለኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ ብር 37,000
- ለኢንተርኔትና ስልክ አገልግሎት ክፍያ ብር 336,000
- ለኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ ብር 52,000
- ለአገር ውስጥ ሥልጠና ብር 50,000

ድምር ብር **32,871,200**

5.3 የውጪ ዕርዳታ በጀት ፍላጐት ማጠቃለያ

በ1996/97 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው ሁለት ጥናቶች በጠቅላላው ብር 31,495,925 ከውጪ ዕርዳታ የሚገኝ ሲሆን፣ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል።

5.4 የውጪ ዕርዳታ በጀት በወጪ ዓይነት

- ለውሎ አበል ....................7,767,520
- ለሥልጠና ....................730,002
- ለሴሚናርና ዓውደ ጥናት ....................775,000
- ለትራንስፖርት ክፍያዎች ....................1,334,316
- ለትራንስፖርትና ጥገና ....................3,967,498
- ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ ....................13,563,000
- ለሌሎች ወጪዎች ....................492,823

28,630,159

መጠባበቂያ 2,865,766

ጠቅላላ ድምር 31,495,925

## 6. የ1997 ጥናቶች ግብና መግለጫ

6.1 የጥናቶች ግብ

በ1997 በጀት ዓመት በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም አሥራ ስድስት የተለያዩ ጥናቶችን በአገሪቱ ገጠርና ከተማ በናሙና በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች ላይ ለማካሄድ ታቅዷል። በዚህ ፕሮግራም አማካይነት የሰዉ ኃይል፣ ሎጂስቲክስና በጀትን በማቀናጀት ከሚካሄዱት ጥናቶች መካከል የግብርና ናሙና ጥናት (የትንበያ፣

የዋናው መኸርና የእንስሳት ጥናቶች) የበልግ ወቅት የግብርና ጥናት፣ የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት፣ የአትክልት፣ ሥራሥርና ቋሚ ሰብሎች የምርታማነት ጥናት፣ የ1996 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ የሰው ኃይል ጥናት፣ የጎዳና ተዳዳሪ ህፃናት ጥናት፣ ወላጅ አልባ ሕፃናት ጥናትና የዋጋ ጥናት የመረጃ መሰብሰብና የመረጃ ቅንብር ሥራ የሚከናወንላቸውና ውጤታቸው ለተጠቃሚዎች በአብዛኛው በበጀት ዓመቱ የሚሰራጭ ሲሆን የጥቂቶቹ ወደሚቀጥለው በጀት ዓመት የሚዛወር ነው።

6.2 የጥናቶች ዝርዝር መግለጫ

6.2.1 የግብርና ስታቲስቲክስ ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

ሀ. የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት

የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ዓላማዎች

የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ከጳጉሜ 4 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ መስከረም 30 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ ባሉት ቀናት የአገሪቱ ክልሎች በሙሉ በሚሸፍን መልኩና በናሙና በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች በገጠር የሚካሄድ ሲሆን፤ የጥናቱ ዓላማም፣

- በምርት ዘመኑ ሊገኝ የሚችለዉን ምርት ሣይንሣዊ በሆነ መንገድ በመገምገምና በምርት ዘመኑ ሊመረት የሚችለዉን ጠቅላላ የጊዜያዊ ሰብል ምርት መጠን ከመኸር ወቅት በፊት በመገመት በዋናዉ መኸር ወቅት በአገሪቱ ሊመረት የሚችለዉን የጊዜያዊ ሰብል ምርት መጠን አስቀድሞ ለመተንበይ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት፣ እና

- በምርት ዘመኑ ትርፍ ሊያመርቱ የሚችሉትንና የምርት እጥረት ሊያጥማቸዉ የሚችሉትን ክልሎችና ዞኖች መለየት የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት ናቸዉ።

በሰብል ምርት ትንበያ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

- የታረሰ መሬት ስፋት በሰብል ዓይነት፣
- የሚጠበቀዉ የምርታማነት ለዉጥ ከ1996 ዓ.ም ምርት በሰብል ዓይነት ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር፣ እና
- ለምርታማነት መቀነስ ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸዉ።

ሰ. የግብርና ናሙና ጥናት

## የግብርና ናሙና ጥናት ዓላማዎች

- በሀገሪቱ በ1997 ሰብል ዘመን የተመረተዉ ጠቅላላ የሰብል ምርት መጠን (ጊዜያዊና ቋሚ ሰብሎችን) በሰብል ዓይነት ለማወቅ፣ በክልሎችና በዞኖች ደረጃ ያለዉን የምርት ሁኔታ ለማወቅ፣ ለማወዳደርና ለማነፃፀር የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት፤

- ከአንድ ሄክታር በሰብል የተያዘ መሬት ላይ የሚገኘዉን ምርትና ምርታማነት ምን ያህል እንደሆነ እንደዚሁም በክልሎችና በዞኖች መካከል ያለዉን ምርትና ምርታማነትን ለማወዳደር የሚረዱ መረጃዎችን ለማግኘት፤

- በ1997 ሰብል ዘመን በሀገር ደረጃ የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን በዋናዉ መኸርና በበልግ በመለየት በሰብል ዓይነት ከ1996 ሰብል ዘመን ሁኔታ ጋር ሲወዳደር የታየዉን ለዉጥ ለመገምገም የሚያስችሉ መረጃዎች ለማግኘት፤

- በ1997 ሰብል ዘመን በዋናዉ መኸርና በበልግ ወቅቶች የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ማለትም ጥቅም ላይ የዋለ የማዳበሪያ ዓይነትና መጠን፣ የምርጥ ዘርና ፀር ሰብል መድኃኒት ዓይነትና መጠን፣ እንደዚሁም የመስኖ አጠቃቀም... ወዘተ ለማወቅ የሚረዱ መረጃዎች ለማግኘት፤

- በሀገሪቱ በገጠር በ1997 ሰብል ዘመን ያለዉን የመሬት አጠቃቀም ሁኔታ ማለትም በሰብል የተያዘ መሬት፣ እዳሪ መሬት፣ በግጦሽ የተያዘ መሬት፣ በደን የተሸፈነ መሬት፣ ወዘተ ስፋትና የግብርና ቤተሰቦችና ባለይዞታዎች ብዛትና ሥርጭትን ለማወቅ የሚረዱ መረጃዎችን ለማግኘት፤

- በ1997 ዓ.ም በሀገሪቱ ያለዉን የቤት እንስሳትን በተመለከተ ብዛታቸዉን በዓይነት፣ በፆታና በዕድሜ እንደዚሁም በሚሰጡት አገልግሎት ዓይነት ለመለየት የሚያስችል መረጃ ለማግኘት፤ እና

- ሌሎች ተዛማጅ የግብርናና የዲሞግራፊያዊ ባህርያትን የሚገልጹ መረጃዎች ለማግኘት።

በግብርና ናሙና ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

- የግብርና ቤተሰብ አባላት (ባለይዞታዎች ጨምሮ) ዲሞግራፊያዊ ባህርያት፣
- የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ በዋናዉ መኸርና በበልግ ወቅት፣
  - ጥቅም ላይ የዋለ የማዳበሪያ ዓይነትና መጠን በሰብል ዓይነት፣
  - ጥቅም ላይ የዋለ የዘር መጠንና ዋጋ በዘር ዓይነት፣
  - በመስኖ ውሃ የለማ የታረሰ መሬት ስፋት በሰብል ዓይነት፣
  - የፀረ ሰብል መድኃኒት አጠቃቀምና ዓይነት፣
  - የሰብል መበላሸት ምክንያትና የብልሽቱ መጠን፣
  - የእያንዳንዱ ሄክታር አማካይ የምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት በሰብል ዓይነት፣
  - የመሬት አጠቃቀም መረጃ
    - በሰብል የተያዘ መሬት ስፋት
    - በእዳሪ የተያዘ መሬት ስፋት
    - በግጦሽ የተያዘ መሬት ስፋት
    - በደን የተያዘ መሬት ስፋት
    - በሌላ የመሬት አጠቃቀም የተያዘ መሬት ስፋት
  - የቤት እንስሳትዶ ዶሮ ሀብት ብዛት በዓይነት፣ በዕድሜ በፆታና በሚሰጡት የጥቅም ዓይነት፣
  - የንብ ቀፎዎች ብዛትና ዓይነት እንዲሁም የማር ምርት መጠን፤

## ሐ. የአትክልት፣ሥራ ሥር ተክሎችና የቋሚ ሰብሎች ጥናት

### የጥናቱ ዓላማ

የአትክልት ፣ሥራ ሥር ተክሎችና ቋሚ ሰብሎች ምርት በሄክታር መረጃ ለማግኘት የምንጠቀምበት የሰብል አጨዳ አሠራር ለሌሎች ጊዜያዊ ሰብሎች ከምንጠቀምበት አሠራር ለየት ያለና ተደጋጋሚ ጉብኝትን የሚጠይቅ በመሆኑ ከሌሎች የግብርና ናሙና ጥናቶች ተለይቶ ለብቻው በሚመደቡ የመስክ መረጃ ሰብሳቢዎችና መስክ ተቆጣጣሪዎች መሠራት ያለበት መሆኑ ግንዛቤ ተወስዷል:: በመሆኑም አስተማማኝ የሆነ ምርት በሄክታር መረጃ ከላይ ለተጠቀሱት የሰብል ዓይነቶች ለማግኘት ይህ የአትክልት፣ ሥራ ሥር ተክሎችና ቋሚ ሰብሎች ጥናት በሁሉም ክልሎች በናሙና በሚመረጡ 100 ያህል ቆጠራ ቦታዎች ይካሄዳል::

በጥናቱ የሚሰበሰቡ የመረጃዎች ዓይነት

በዚህ ጥናት ጥናቱ ለሚመለከታቸው አትክልቶች ሥራ ሥር ተክሎችና ቋሚ ሰብሎች ከአንድ ሄክታር (Yield per hectar) ወይም ከአንዱ ዛፍ (Yield per tree) ሊገኝ የሚችለውን የምርት መጠን (ምርታማነት) ሊያስገኝ የሚችል መረጃ በሰብል አጨዳ አሠራር(Crop-Cutting experiment) ይሰበሰባል:: በተጓዳኝም የማሳ ስፋትና የቋሚ ሰብሎች እግር ብዛት መረጃ ይሰበሰባል::

## 6.2.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ጥናት ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

### ሀ. የአምራቾች ዋጋ ጥናት

የአምራቾች ዋጋ ጥናት ዓላማዎች

የአምራቾች ዋጋ ጥናት በገጠር በየወሩ የሚሰበሰብ ሲሆን የጥናቱ አበይት ዓላማዎች፣

- ፖሊሲ አዉጪዎች ስለእርሻ ዉጤቶች ምርትና ሥርጭት አስመልክቶ ዉሳኔ ለመስጠት የሚረዱ መረጃዎች፣
- ገበሬዎች በአምራቾች ደረጃ ለእርሻ ዉጤቶች የሚያስከፍሉትን ዋጋ መጠን ለማጥናት መሠረት የሆኑ መረጃዎች፣
- የምርት ጠቅላላ ዋጋና የሀገር ሀብት ዉጤትን ለማስላት የሚረዱ እንደዚሁም በኢኮኖሚዉ ላይ የሚታየዉን ለዉጥ ለማጥናት መነሻ የሚሆኑ መረጃዎች፣
- የእርሻ ዉጤቶችን በሚመለከት የአምራች ዋጋን የምርት መጠን መመዘኛ ኢንዴክሶችን ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ መረጃዎች መሰብሰብ ናቸዉ::

በአምራቾች ዋጋ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

ለአምራቾች ዋጋ ጥናት በገጠር በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች የግብርና ዉጤቶች የአምራች ዋጋ መረጃ የሚሰበሰብ ሲሆን እነዚህም የእህል፣ የጥራጥሬ፣ የቅባት እህሎች፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የቅመማ ቅመም፣ የወተትና የወተት ተዋፅኦ፣ እንቁላል፣ የቁም ከብቶች፣.... ወዘተ የዋጋ መረጃዎች ይሰበሰባሉ::

## ለ. የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት

### የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ዓላማዎች

የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በከተማ የሚገኙ 120 ትላልቅ ገበያዎች የሚሰበሰብ ሲሆን የጥናቱ ዋና ዓላማዎች፡-

- የችርቻሮ ዋጋ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ማወቅ፣
- በተለያዩ የሥርጭት ደረጃዎች መካከል ያሉትን የዋጋ ልዩነቶች ለማወቅ፣
- በኢኮኖሚዉ ላይ የሚታየዉን ለዉጥ ለመገምገም፣
- ለቤተሰብ ፍጆታ የዋሉትን ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋ ለመተመን፣
- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ምርትና ስርጭት በሚመለከት ፓሊሲ አዉጪዎች ዉሳኔ ለመድረስ የሚያስችሉ መነሻ መረጃዎች ለማግኘት፣
- የምርትን ጠቅላላ ዋጋና የሀገር ሀብት ዉጤትን ለማስላት እንደዚሁም የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ለማዘጋጀት የሚያስችሉ መረጃዎች መሰብሰብ ናቸዉ፡፡

በችርቻሮ ዋጋ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት፡-

ለችርቻሮ ዋጋ ጥናት በከተማ ከተመረጡ ትላልቅ ገበያዎች / በዋና ዋና የመገበያያ ሥፍራዎች /የእርሻና የኢንዱስትሪ ዉጤቶች ከግል ነጋዴዎች የችርቻሮ ዋጋ መረጃ የሚሰበሰብ ሲሆን እነዚህም የምግብ፣ የመጠጥ፣ የትምባሆ፣ የልብስ፣ የጫማ፣ የሕንፃ መሣሪዎች፣ የቤት ኪራይ፣ የቤት መገልገያ ዕቃዎች፣ የሕክምና መድኃኒት፣ የመጓጓዣ፣ የትምህርት፣ የመዝናኛ፣ የእርሻ መገልገያ መሣሪያዎች፣ የሆቴል ምግብና አልጋ፣... ወዘተ የዋጋ መረጃዎች ናቸዉ፡፡

## ሐ. የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት (ሁለተኛ ዙር)

### የጥናቱ ዋና ዋና ዓላማዎች

- የድህነት ወለልን /መስመርን/ ለመወሰን የሚያስች መረጃዎችን ማስገኘት፣
- የቤተሰቦችን የገቢና ወጪ ስርጭት ለማጤን፣
- ከምግብ ፍጆታ የሚያገኘውን የኃይል መጠን /Calorie/ ለመገመት የሚያስችል መረጃ ማስገኘት፣
- የዋጋዎች አመልካች የሆነውን የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ለማዘጋጀት አስፈላጊ የሆነውን የወጪ ድርሻ ለማግኘት እን በኢንዴክሱ የሚካተቱ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ለመወሰን፣

- በሀገር ሀብት ግመታ /National accounts aggregates/ የቤተሰቦችን አጠቃላይ ወጪ ለማስላት እና፣
- እነዚህን መረጃዎች በማጤን ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን ለመቅረጽ፣ ለመከታተልና በቤተሰቦች፣ በግለሰቦችና አጠቃላይ ማሕበረሰቡ ላይ የሚያስከትለውን ለውጥ ለማጤን ያስችላል::

በጥናቱ የሚሰበሰቡ መረጃ ዓይነቶች

- የምግብና መጠጦች ፍጆታ ሁኔታ፣
- የቤተሰብ ወጪዎች በወጪ ዓይነትና ምንጭ፣
- የስነ-ህዝብ ባህሪያትና የስራ ሁኔታ እና ሌሎች በርካታ መረጃዎች ይገኙበታል::

መ. ተሳትፏዊ የድህነት ሁኔታ ዳሰሳ ጥናት

የጥናቱ ዓላማ

ተሳትፏዊ በሆነ መንገድ ወይም ዘዴ የድህነትን ሁኔታ ለማጥናት የሚያስችል መረጃ ለመንግስትና ለመረጃ ተጠቃሚዎች ለማቅረብ ሲሆን፣ ዋና ዋና ዓላማዎቹም፣

- የድህነት ገጽታዎችንና መንስኤዎችን ለመዳሰስ፣
- አገሪቱ ለምትቀርጻቸው የድህነት ቅነሳ ፖሊሲዎች ጠቃሚ ግብዓቶችን ለማግኘት፣
- ዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራምን በተመለከተ ሕብረተሰቡ ላይ ያስከተለውን ለውጥ ለመገምገም፣

ከጥናቱ የሚሰበሰቡ የመረጃ ዓይነቶች

- ስለ መልካም አስተዳደር
- ስለ ሰው ኃይል ልማት
- አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያን በሚመለከት
- ለአደጋዎች/ለችግሮች የመጋለጥ ሁኔታን በሚመለከት

### 6.2.3 የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ ጥናት ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

#### ሀ. የትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት

በዚህ ጥናት አሥርና ከአሥር በላይ ሠራተኞች ከሚያሰማሩ፣ በአንድ ሥፍራ የተለየ አድራሻ ካላቸዉ፣ አብዛኛዉ ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ ሆኖ በኢነርጂ ወይም በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ መሣሪያ በመጠቀም አንድ ወይም የተለያዩ ምርቶችን ከሚያመርቱ

ፋብሪካዎች ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የሚሰበሰቡ ሲሆን ጥናቱ የሚካሄደዉም በከተማዎች ክልል ነዉ፡፡

## የትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ዓላማ፣

- የዘርፉን ዕድገት በሚመለከት የኢኮኖሚ ፖሊሲና የልማት ዕቅድ አዉጪዎች እንደዚሁም ተመራማሪዎች በመነሻነት የሚጠቀሙበት ስታቲስቲካዊ መረጃ በኢንዱስትሪና በባለቤትነት ዓይነት ለማቅረብ፣

- ዘርፉ ያስማራዉን የሰዉ ኃይልና የምርት መጠን ለማወቅና ለሀገር ሀብት ዉጤት የሚያበረክተዉን ድርሻ ለማስላት አስፈላጊ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለማግኘት፣

- ዘርፉ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች በተለይም ከግብርናዉ ጋር ያለዉን መስተጋብር እንዲሁም ከዉጭ ጥሬ ዕቃዎችን በማስገባት በኩል ያለዉን ድርሻ ለመገመት የሚያስችሉ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በዝርዝር መሰብሰብ ናቸዉ፡፡

## ከትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

- የፋብሪካዉ ሕጋዊ አቋም፣
- የተከፈለ ካፒታል መጠን ( Paid -up - Capital)፣
- የሠራተኞች ብዛት፣ ደመወዝና ምንዳ ፣
- የምርት መጠንና ዋጋ፣
- የጥሬ ዕቃ ፍጆታ ፣
- ልዩ ከማምረት ይዘት ጋር የተዛመዱና ያልተዛመዱ ወጪዎች፣
- የቋሚ ንብረት ዓይነትና በቋሚ ንብረት ላይ የተደረገ የመዋዕለ ንዋይ መጠን፣
- የማምረት ችሎታ፣ ... ወዘተ አመልካች መረጃዎችን ይሰበሰባሉ፡፡

## ለ. የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የምርት፣ መጠንና የአምራቾች ዋጋ ጥናት/ በከተማ/ የጥናቱ ዋና ዋና ዓላማዎች

ጥናቱ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች በሙሉ /ትላልቅና መካከለኛ/ የሚሰበሰብ ሲሆን፤ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

- ፖሊሲ አዉጪዎች ስለኢንዱስትሪ ዉጤቶች ምርትና ስርጭት ለሚወስዱት ዉሣኔ እንዲረዳ፣
- ባለፋብሪካዎች በአምራች ደረጃ ለኢንዱስትሪ ዉጤቶች የሚያስከፍሉትን የዋጋ መጠን ለማጥናት፣
- የምርትን ጠቅላላ ዋጋና የሃብት ዉጤትን ለማስላት የሚረዱ እንደዚሁም በኢኮኖሚዉ ላይ የሚታየዉን ለዉጥ ለማጥናት መነሻ የሚሆን መረጃ ለማግኘት፣
- በተለያዩ የስርጭት ደረጃዎች ያሉትን የዋጋ ልዩነቶች ለማጥናት፣
- የኢንዱስትሪ ዉጤቶችን በሚመለከት የአምራች ዋጋ ኢንዴክሶችን ለማዘጋጀት እንዲያገለግል ነዉ፡፡

### የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

- የአምራቾች ሙሉ አድራሻ ፣
- የምርት መጠን፣ እና
- የአምራች መሸጫ ዋጋ ናቸው፡፡

## ሐ. የቢዝነስ ድርጅቶች ምዝገባ ሥርዓትን የማደራጀትና ወቅታዊ የማድረግ ሥራ የጥናቱ ዓላማ

- የቢዝነስ ምዝገባ ሥርዓቱ በየጊዜው ለሚካሄዱ የናሙና ጥናቶችና አጠቃላይ ቆጠራዎች ለመነሻነት የሚያገለግሉ መረጃ /Master File of Establishment/ Enterprises/ ለማደራጀትና
- የአገሪቱን የኢኮኖሚ ድርጅቶች አስመልክቶ የመረጃ ክምችት / Databases/ ለመፍጠር፣

- በየጊዜው ለሚካሄዱ አጠቃላይና ዝርዝር የኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች የናሙና ጥናቶች፣ ለወቅታዊ የኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ጥናቶች እና ለዋጋ፣ ለምርትና ለአገልግሎት መመዘኛ ኢንዴክሶች የመነሻ የድርጅቶች ዝርዝር / Basic frames/ በማጠናቀርና በየዓመቱ በማደስ Up-date በማድረግ/ የናሙና መሠረት ለማስገኘት፣

- የአገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ድርጅቶች ብዛትና ሥርጭት በምርት፣ በንግድና በአገልግሎት ዓይነት፣ በክልል፣ በአሰማሩት የሰው ኃይል፣ በዓመታዊ ገቢ.....ወዘተ ለማወቅ የሚያስችል የተቀነባበረ መረጃና ትንታኔ በየጊዜው ለመረጃ ተጠቃሚዎች ለማቅረብ፣
- ለብሔራዊ አካውንት ስታቲስቲክስ ስሌት ግመታ /Estimation/ መሰረት የሆኑ መረጃዎችን ለማስገኘት የሚያስችል ይሆናል፡፡

የቢዝነስ ምዝገባ ሥርዓቱ የሚሰበስቡ መረጃዎች

የቢዝነስ ድርጅቶችን አቋማዊ መረጃ /Structural Information/ ሊያመለክቱ የሚችሉ ማለትም፣ የድርጅቶች ስም፣ አድራሻ የባለቤትነት ዓይነት፣ ሥራ የጀመሩበት ጊዜ፣ የምርት፣ የንግድ ወይም የአገልግሎት ዓይነት፣ የባለቤቶች ብዛት በፆታ፣ የአሰማሩት የሰው ኃይል፣ የሂሳብ መዝገብ ሁኔታ፣ ካፒታል፣ ዓመታዊ ገቢ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

መ. <u>ወቅታዊ የማምረቻ፣ የንግድና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት፣</u>
<u>የጥናቱ ዓላማዎች:-</u>

- የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ሊያመለክቱ የሚችሉ መረጃዎችን ተከታታይነትና ወጥነትን ባለው መልኩ በየጊዜው ለማቅረብ፣

- የኢኮኖሚ ዕቅድና ፖሊሲ አውጪዎች፣ ተመራማሪዎችና ኢንቨስተሮች ወቅታዊ የአገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት የሚያመለክቱ መረጃዎችን እንዲያገኙ ለማድረግ፣ እና

- ለወቅታዊ የብሔራዊ አካውንትስ ስሌት ግባት የሆኑ መረጃዎች ለማቅረብ ናቸው፡፡

የሚሰበሰቡ የመረጃዎች ዓይነት

በምርት፣ በንግድ እና በአገልግሎት ዘርፎች የተሰማሩ ድርጅቶች ብዛትና ሥርጭት፣ ያስማሩት የሰው ኃይል፣ ካፒታል፣ ገቢ፣ የተለያዩ ወጪዎች፣ ድርጅቶች ያጋጠሙዋቸው ችግሮች ዓይነት፣ የማምረት አቅምና የመሳሰሉት ዋና ዋና መረጃዎች ይሰበሰባሉ።

6.2.4 የማሕበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናት ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች

ሀ. የሰው ኃይል ጥናት

የጥናቱ ዋና ዋና ዓላማዎች:

- ሀገሪቱ ያላትን ለስራ የደረሰና ለሥራ ዝግጁ የሆነ የሰው ኃይል (Active Population) እና በተለያየ ምክንያት በስራ ላይ ሊሠማራ የማይችለው (Inactive Population) የሰው ብዛት በተመለከተ ስታቲስቲካዊ መረጃ ለማስገኘት፣
- በጥናቱ ወቅት በስራ ላይ የተሰማራው (Employed population) ብዛት እና ስራ የሌላቸው ሰዎች(Unemployed population) መጠን ለማግኘት፣
- ከስራ ላይ የተሠማራው የሰው ኃይል /employed population/ መሠረታዊ ባህርያትን ለማጥናት፣
- የሥራ አጡን ባህርያትና ስርጭት ለማወቅ፣
- ሀገሪቱ ያላትን የሰለጠነ የሰው ኃይል ብዛትና በምን ሙያ እንደሰለጠነ ለማጤን፣
- ለወደፊቱ ለተከታታይ ጥናትና ለትንበያ የሚረዱ መረጃዎችን ለማስገኘት፣
- ለመንግስት ፖሊሲና ዕቅድ አውጪዎች ለግል ተመራማሪዎች ለሌሎች ተጠቃሚዎች ፣ የመረጃ ፍላጎታቸውን ለማርካት፣
- በቅጥር ሥራ የተሰማራውን የሰው ኃይል የደሞዝና ምንዳ መረጃ ለማስገኘት፣

## በጥናቱ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

- ዲሞግራፊያዊ መረጃዎች (ስም፣ ዕድሜ ፣ ፆታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የትምህርት ደረጃና የሙያ ዓይነት እና የፍልሰት ሁኔታ)
- የሥራ ስምሪት ሁኔታ Engagement in Employment፣ ባለፉት 12 ወራትና ባለፉት ሰባት ቀናት፣
- በምርታማ ሥራ ስለመሰማራት (Engagement in Productive Activity)
- በምርታማ ሥራ የተሰማሩትን በሚመለከት (Employment)
    - የተሰማሩበት ዋነኛ የሥራ መስክ /ዓይነት/፣
    - በዋነኛነት የተሰማሩበት ድርጅት (የቤተሰብ) የግለሰብ ወይም የመንግስት) ምርት ወይም አገልግሎት ዓይነት) ፣
    - በዋነኛነት በተሰማሩበት የሥራ መስክ የቅጥር ሁኔታ፣
    - ከዋነኛ ሥራቸው በተጨማሪ ስራ ስለመሥራታቸው (Additional Employment)፣
    - ተጨማሪ ሥራቸውን በምን መንገድ እንዳገኙት፣
    - የተጨማሪ ሥራቸው ዓይነት፣
    - ተጨማሪ ሥራቸውን የሚያከናውኑበት ድርጅት ምርት ወይም አገልግሎት ዓይነት፣
    - በተጫማሪ ሥራቸው የቅጥር ሁኔታ፣
    - በጠቅላላው (በሁሉም ሥራዎች) የሰሩት የሥራ ሰዓት መጠን እና የገቢ (የክፍያ) መጠን፣
- በጠቅላላው ያገኙት የገቢ መጠን በቂ ስለመሆኑ፣
- ከፊል ሠራተኝነት (**Underemployment**)
    - የሠሩት የሥራ ሰዓት መጠን በቂ ስለመሆኑ፣
    - የሠሩት የሥራ ሰዓት መጠን በቂ ያልሆነበት ምክንያት፣
    - በተጨማሪ በምን ሥራ መሰማራት እንደሚፈልጉ፣
    - ተጨማሪ ለምን ያህል ሰዓት መሥራት እንደፈለጉ፣
    - በተጨማሪ መሥራት የፈለጉበት ዋናው ምክንያት፣
- በምርታማ ሥራ ያልተሰማሩትን በሚመለከት (Unemployment)
    - በምርታማ ሥራ ያልተሠማሩበት ምክንያት፣
    - ከዚህ ቀደም ሥራ ሰርተው ያወቁ እንደነበር፣
    - ከነበረ የመጨረሻው የሥራ ዓይነት፣
    - ከመቼ ጀምሮ ሥራውን መሥራት እንዳቆሙ፣
    - ለምን የቀድሞውን ሥራ መሥራት እንዳቆሙ፣

- ስራ በመፈለግ ላይ ስለመሆናቸው፣
- በምን መንገድ ሥራ እየፈለጉ እንደሆነ፣
- ለምን ያህል ጊዜ ሥራ እንደፈለጉ ፣
- እስካሁን ሥራ ያላገኙበት ምክንያት፣
- ምን ዓይነት ሥራ እንደሚፈልጉ፣

ለ. <u>የወላጅ አልባ ህፃናት ጥናት</u>

<u>የጥናቱ ዓላማ</u>

በአገሪቱ ዉስጥ ያለዉን የወላጅ አልባ ህፃናት ብዛትና ያሉባቸዉን ችግሮች በመለየት ለዕቅድና ፕሮግራም አዉጪዎች ማቅረብ።

- በአገሪቱ ገጠርና ከተማ የወላጅ አልባ ህፃናት መጠንና ዲሞግራፊያዊ ባህርያት ለማወቅ፣
- የወላጅ አልባ ልጆች ወላጆቻቸዉን የሞቱበትን ምክንያት ለማወቅ፣
- ወላጅ አልባ ህፃናት በአሁኑ ወቅት ያሉባቸዉን ችግሮች ለማወቅ፣
- የወላጅ አልባ ህፃናትን አኗኗር፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባህርይ ለመዳሰስ፣
- HIV/AIDS ስርጭት በወላጅ አልባነት ላይ ያመጣዉን ተፅዕኖ ለመለየት፣

<u>በጥናቱ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

- የልጆች ወላጆች በህይወት መኖር አለመኖር /እናት/ አባት/
- የልጆች ስምና ዕድሜ፣
- ልጆች ከኃላፊ ጋር ያላቸዉ ዝምድና
- የልጆች የቀድሞ መኖሪያ ቦታ ገጠር/ከተማ
- የትኛዉ ወላጅ እንደሞተ /ቱና መቼ እንደሞተ/ቱ ወር፣ ዓ.ም
- ወላጆቹ ሲሞቱ እድሜዉ ስንት እንደነበር፣
- ወላጆቹ በምን ሰበብ እንደሞቱ፣ (አደጋ፣ HIV/AIDS እርግጠኛ፣ HIV/AIDS ጥርጣሬ/ወሬና ሌላ በሽታ)
- ወላጆች ከመሞታቸዉ በፊት የነበራቸዉ የጋብቻ ሁኔታ፣የትምህርት ደረጃ፣ የገቢ ምንጭና የኢኮኖሚ ደረጃ፣
- አሁን በህይወት ያለ ወላጅ (ካለ) የጋብቻ ሁኔታ፣የትምህርት ደረጃ፣ የገቢ ምንጭና የኢኮኖሚ ደረጃ፣

- ልጆች እርዳታ ያገኙ እንደሆነ የእርዳታዉ ሁኔታ፣
- የልጆቹ የትምህርት ሁኔታ፣ ከአሳዳጊዎቻቸዉ ጋር ያላቸዉ ግንኙነት፣
- ያሉባቸዉ ችግሮች፣የሥራ ሁኔታ፣የጤንነት ሁኔታ፣ ስለራሳቸዉ ያላቸዉ ተስፋ፣
- ወደፊት ምን መሆን እንደሚያስቡ፣
- ልጆቹ ስለአካባቢ/ ስለማህበረሰቡ ያላቸዉ አመለካከት፣
- ሌሎች፤

ሐ. <u>የጎዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ጥናት</u>

<u>የጥናቱ ዓላማ</u>

- በአገሪቱ በተለያዩ ከተሞች የሚገኙትን የጎዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ብዛት፣ዲሞግራፊያዊ፣ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ባህርያት እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ያሉባቸዉ የተለያዩ ችግሮችን በሚመለከት የተሟላ መረጃ ለመሰብሰብ፣
- የጎዳና ተዳዳሪነት መስፋፋት ዋና ዋና መንስኤዎችን ለማጥናት፣
- በጎዳና ተዳዳሪዎች አገልግሎት በመስጠት፣ድጋፍና እንክብካቤ በማድረግ ላይ የሚገኙ ድርጅቶች ብዛታቸዉን፣ የሚሰጡትን አገልግሎት ዓይነትና በአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሆኑ ሕፃናትን በሚመለከት የተሟላ መረጃ ለመሰብሰብ፣
- የጎዳና ተዳዳሪዎች ችግርን ለመቅረፍ በመንግስት በኩል እስካሁን የተወሰደዉን እርምጃ በመገመገም ወደፊት በዚህ ረገድ መወሰድ ስለሚገባቸዉ እርምጃዎች ለፕላነሮችና ለፖሊሲ አዉጪዎች ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ለማቅረብ፣

<u>በጥናቱ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

- የጎዳና ተዳዳሪዎች መኖሪያ አካባቢ መረጃ፣
- የጎዳና ተዳዳሪዎች ዲሞግራፊያዊ ባህርያት፣
- የጎዳና ተዳዳሪዎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ባህርያት (ትምህርት፣የሥራ ሁኔታና የጤና ሁኔታ)
- ኤች.አይ.ቪ. ኤይድስንና የአባለዘር በሽታን በሚመለከት ያላቸዉ ዕዉቀትና ዝንባሌ፣

- የጎዳና ተዳዳሪዎች የአመጋገብ ሁኔታ፣የመኝታ ሁኔታ፣ ከቤተሰብ ወይም ከአሳዳጊዎቻቸዉ ጋር ያላቸዉ ግንኙነት፣
- የጎዳና ኑሮ/ሥራ አጀማመር ሁኔታ፣
- የጎዳና ተዳዳሪዎች የተለያዩ ሱሶች (ልምድ) ተገዥነት፣ ወይም ወንጀል የመፈጸም ሁኔታ፣ የወደፊት ዕቅድና ፍላጎት፣ ስለማህበረሰቡ ያላቸዉ አመለካከት፣ ከአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጋር ያላቸዉ ግንኙነት፣

ከአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች (መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ)

- የጎዳና ተዳዳሪዎች አገልግሎት ድጋፍና እንክብካቤ
  - ለጎዳና ተዳዳሪዎች በአጠቃላይ የሚደረግ ድጋፍና እንክብካቤ፣
  - በኤይድስ ለተጠቁ ጎዳና ተዳዳሪዎች በተለይ የሚደረግ ድጋፍና እንክብካቤ፣
  - ለሴት ጎዳና ተዳዳሪዎች በተለይ የሚደረግ ድጋፍና እንክብካቤ፣
  - ለወላጅ አልባ ጎዳና ተዳዳሪዎች በተለይ የሚደረግ ድጋፍና እንክብካቤ፣
  - የአካል ጉዳተኛ ለሆኑ ጎዳና ተዳዳሪዎች በተለይ የሚደረግ ድጋፍና እንክብካቤ፣
- ብዛታቸዉ፣ መቼ እንደተቋቋሙ፣ የሚሰጡት አገልግሎት ዓይነት፣
- የአገልግሎታቸዉ ሽፋን በአገልግሎት ዓይነትና በጂኦግራፊያዊ አካባቢ፣ ዉጤታማ የነበሩ ፕሮግራሞቻቸዉ ዓይነት (Area of Intervention Succeeded)
- ዉጤታማ ያልነበሩ ፕሮግራሞቻቸዉን በሚመለከት ለምን ዉጤታማ እንዳልነበሩ (Area of Interventions Failed, Why?)

ከቤተሰብ

- ዲሞግራፊያዊ ባህርያት፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ባህርያት፣
- ጎዳና ተዳዳሪነትን በሚመለከት ያላቸዉ ግንዛቤና አመለካከት፣
- የጎዳና ተዳዳሪነትን ችግር ለመቅረፍ ወደፊት መወሰደ ስለሚገባዉ እርምጃ ያላቸዉ አስተያየት፣

## 7. የ1997 የሰው ኃይል ፍላጎት

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1997 በጀት ዓመት የሚያከናውናቸውን ጥናቶች ተግባራዊ ማድረግ 1,450 ከሚጠጉ ቋሚ ሠራተኞች በተጨማሪ የሚያስፈልገው የሰው ኃይል 11,143 ሲሆን፣ ዝርዝሩም በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል።

የ1997 የሰው ኃይል ፍላጎት

| ተ.ቁ | የሠራተኛው ሁኔታ | የሰው ኃይል ፍላጎት | |
|---|---|---|---|
| 1 | በሙያ ዓይነት | | |
| 1.1 | የሰለጠነ | 75 | ለ 12 ወራት |
| 1.2 | በከፊል የሰለጠነ | 1,880 | ለ 7 ወራት |
| 1.3 | " " | 263 | ለ 10 ወራት |
| 1.4 | " " | 320 | ለ 12 ወራት |
| 1.5 | " " | 2,565 | ለ 1.5 ወራት |
| 1.6 | ያልሰለጠነ | 119 | ለ 12 ወራት |
| 1.7 | " " | 790 | ለ 2 ወራት |
| 1.8 | " " | 5,131 | ለ 1.5 ወራት |
| | ድምር | 11,143 | |
| 2 | በቅጥር ዓይነት | | |
| 2.1 | ቋሚ | - | |
| 2.2 | ኮንትራት | 5,103 | |
| 2.3 | ጊዜያዊ | 6,040 | |
| | ድምር | 11,143 | |

## 8. የ1997 የጥናቶች መርሃ-ግብር

ጥናቶች በአንድ ወቅት ተጀምረው በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መጠናቀቅ ስላለባቸው መከናወን የሚገባቸው ዝርዝር ተግባራት በወቅቱ እንዲከናወኑና የሥራው እንቅስቃሴ የደረሰበትን ደረጃ ለመከታተልና ለመቆጣጠር ይቻል ዘንድ የድርጊት መርሃ-ግብር ማዘጋጀት አስፈላጊና ወሣኝ ነው። በመሆኑም የ1997 በጀት ዓመት ጥናቶች አፈፃፀም ወርሃዊ የሥራ መርሃ-ግብር እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል።

# የ1997 በጀት ዓመት ጥናቶች መርሃ-ግብር

ሠንጠረዥ 1

| ተ. ቁ | የሥራዉ ዓይነት | ሥራዉ | |
|---|---|---|---|
| | | የሚጀመርበት | የሚጠናቀቅበት |
| 1 | የሰብል ትንበያ ጥናት | | |
| 1.1 | የዝግጅት ሥራ | | |
| | - የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | ግንቦት 15/1996 | ሐምሌ 10/1996 |
| | - የአሠልጣኞች ሥልጠና በዋናዉ መ/ቤት | ሐምሌ 10/1996 | ሐምሌ 25 /1996 |
| | - የመስክ ሠራተኞች ሥልጠናና ሥምሪት | ነሐሴ 1/1996 | ነሐሴ 30/1996 |
| 1.2 | መረጃ መሰብሰብ | ጳጉሜን 4/1996 | መስከረም 25/1997 |
| 1.3 | ዶክመንቶች ወደዋናዉ መ/ቤት ማሰባሰብ | መስከረም 30/1997 | ጥቅምት 5/1997 |
| 1.4 | የመረጃ ቅንብር | | |
| | - የኤዲቲንግና ኮዲንግ | ጥቅምት 6/1997 | ጥቅምት 20/1997 |
| | - የዳታ ኢንትሪ ሥራ | ጥቅምት 10/1997 | ጥቅምት 25/1997 |
| | - የዳታ ክሊኒንግ ሥራ | ጥቅምት 15/1997 | ጥቅምት 27/1997 |
| | - ታቡሌሽን | ጥቅምት 28/1997 | ኅዳር 10/1997 |
| 1.5 | ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት | ጥቅምት 20/1997 | ኅዳር 20/1997 |
| 2 | የግብርና ናሙና ጥናት በዋናዉ መኸር | | |
| | • የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን ጥናት | | |
| 2.1 | የዝግጅት ሥራ | | |
| | - የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | ግንቦት 15/1996 | ሐምሌ 10/1996 |
| | - የአሠልጣኞች ሥልጠና በዋናዉ መ/ቤት | ሐምሌ 10/1996 | ሐምሌ 25 /1996 |
| | - የመስክ ሠራተኞች ሥልጠናና ሥምሪት | ነሐሴ 1/1996 | ነሐሴ 30/1996 |
| 2.2 | መረጃ መሰብሰብ | ጳጉሜን 4/1996 | ጥር 30/1997 |
| 2.3 | ዶክመንቶች ወደዋናዉ መ/ቤት ማሰባሰብ | | |
| | - የመሬት ስፋት | ታህሣስ 1/1997 | ታህሣስ 15/1997 |
| | - የአጨዳ ውጤት | የካቲት 11/1997 | የካቲት 20/1997 |
| 2.4 | የመረጃ ቅንብር | | |
| | - የኤዲቲንግና ኮዲንግ | ታህሣሥ 12/1997 | የካቲት 30/1997 |
| | - የዳታ ኢንትሪ ሥራ | ታህሣሥ 20/1997 | መጋቢት 10/1997 |
| | - የዳታ ክሊኒንግ ሥራ | ጥር 15/1997 | መጋቢት 10/1997 |
| | - ታቡሌሽን | የካቲት 1/1997 | መጋቢት 20/1997 |
| 2.5 | ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት | ጥር 15/1997 | ሚያዝያ 5/1997 |

| ተ.ቁ | የሥራዉ ዓይነት | ሥራዉ | |
|---|---|---|---|
| | | የሚጀመርበት | የሚጠናቀቅበት |
| 3 | የግብርና ናሙና ጥናት በዋናው መሸር | | |
| | • የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ | | |
| 3.1 | <u>የዝግጅት ሥራዎች</u> | | |
| | - የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | ግንቦት 15/1996 | ሐምሌ 10/1996 |
| | - የአሠልጣኞች ሥልጠና በዋናዉ መ/ቤት | ሐምሌ 10/1996 | ሐምሌ 25/1996 |
| | - የመስክ ሠራተኞች ሥልጠናና ሥምሪት | ነሐሴ 1/1996 | ነሐሴ 30/1996 |
| 3.2 | መረጃ መሰብሰብ | ጳጉሜን 4/1996 | ኅዳር 28/1997 |
| 3.3 | ዶክመንቶች ወደዋናዉ መ/ቤት ማሰባሰብ | ታህሣሥ 1/1997 | ታህሣሥ 10/1997 |
| 3.4 | የመረጃ ቅንብር | | |
| | - የኤዲቲንግና ኮዲንግ | ታህሣሥ 5/1997 | ታህሣሥ 1/1997 |
| | - የዳታ ኢንትሪ ሥራ | ታህሣሥ 15/1997 | ጥር 5/1997 |
| | - የዳታ ክሊኒንግ ሥራ | ታህሣሥ 20/1997 | ጥር 10/1997 |
| | - ታቡሌሽን | ጥር 1/1997 | ጥር 20/1997 |
| 3.5 | ሪፖርት ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት | ታህሣስ 15/1997 | ሚያዝያ 30/1997 |
| 4 | የግብርና ናሙና ጥናት በዋናው መሸር | | |
| | • የመሬት አጠቃቀም ጥናት | | |
| 4.1 | የዝግጅት ሥራዎች | | |
| | - የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅትና ሕትመት | ግንቦት 15/1996 | ሐምሌ 10/1996 |
| | - የአሠልጣኞች ሥልጠና በዋናዉ መ/ቤት | ሐምሌ 10/96 | ሐምሌ 25/1996 |
| | - የመስክ ሠራተኞች ስልጠና በዋናዉ መ/ቤት | ነሐሴ 1/1996 | ነሐሴ 30/1996 |
| 4.2 | መረጃ መሰብሰብ | ጳጉሜን 4/1996 | ኅዳር 28/1997 |
